# Learning by Ear 2013

**"መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" – "መዘዙን መቀበል"**

EPISODE 25: **በነገራችን ላይ…**

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Maja Braun, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: አቶ ሙላቱ VISITS ወ/ሮሉሊት AT HOME**

- **ወ/ሮሉሊት (F, 40)**
- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**

**SCENE 2: ብሩክ, ቅዱስ AND MOSY RETURN FROM UPCOUNTRY**

- **ብሩክ (M, 8)**
- **ቅዱስ (M, 8)**
- **ሙሴ (M, 30s)**

**SCENE 3: MRS. ወ/ሮ ዘውዲቱ TALKS TO ወ/ሮሉሊት AT THE MARKET**

- **TRADER 1 (F/M, ADULT)**
- **TRADER 2 (F/M, ADULT)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**
- **CUSTOMER (F, 35)**
- **MRS. ወ/ሮ ዘውዲቱ (F, 35)**

**SCENE 4: ምህረት IS NOT FEELING WELL**

- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**
- **ምህረት (F, 15)**

## **INTRO**

## 1. NARRATOR:

**ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ስለ አፍሪቃውያን ታዳጊ ወጣቶች የሚተርከዉና ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉ ተከታታይ ትምህርታዊ ድራማ ነዉ። ዛሬ "መዘዙን መቀበል"በተሰኘዉ ሁለተኛው ዙር ድራማ ሃያ አምስተኛ ክፍል ላይ ደርሰናል።እስከ ዛሬ ብዙ ነገሮች እንደተከሰቱ በድራማው ያለፉት ተከታታይ ክፍሎች አድምጠናል። ባለፈው ጊዜ የምህረት አባት አቶ ሙላቱ ከፖሊስ ጣቢያ ተለቅቀዋል፡፡ የምህረትን የክፍል ጓደኛ የንጉሴ ጃለታን ቤት በመዝረፍ ተጠርጥረው ለወራት ያህል ታስረው ነበር፡፡ በስተመጨረሻም በዝርፊያው አለመሰማራታቸው ሲታወቅ አቶ ጃለታ እና ወ/ሮ ዘውዲቱ አቶ ሙላቱን ባልዋሉበት በመጠርጠራቸው በጣም ተጸጽተዋል፡፡ መርማሪ ርብቃ አቶ ሙላቱን ስትለቃቸው በሌላ ወንጀል እንደተከሰሱ ግን ነግራቸዋለች፡፡ :**

## 2. EPISODE 24, LINES 28 – 29:

***<u>መርማሪ ርብቃ</u> : የገዛ ልጅህን ለአቶ አቶ መኩሪያ መሸጥህን በማመንህ ትቀጣለህ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ በየቀኑ ፖሊስ ጣቢያ እየተገኘህ መኖርህን ታሳውቃለህ፣ አቶ ሙላቱ፡፡ የአንተን ጉዳይ የሚሰማበት ቀን እናሳውቅሀለን፡፡***

***<u>አቶ ሙላቱ:</u> እሺ፣ ኢንስፔክተር መርማሪ ርብቃ .***

## 3. NARRATOR:

**አቶ ሙላቱ እስር ቤት ውስጥ በነበሩበት ወቅት ባለቤታቸው ወ/ሮሉሊት ነፍሰጡር ሴት ልጃቸውን እና መንትዮቹ ቅዱስን እና ብሩክን ለመመገብ ሲጣጣሩ ነበር፡፡ አሁን ግን የራሳቸውን ስራ ጀምረው የገንዘብ ችግራቸው የተቃለለ ይመስላል፡፡:**

## ***KW BEGIN***

**4. EPISODE 24, LINES 58 - 59:**

*ምህረት፡* እማዬ ያን የአትክልት መሸጫ ከጀመርሽ ጊዜ አንስቶ የምንበላው ስጋ ነው።

*ወ/ሮሉሊት፡* አረንጓዴ ጎመን፣ ስኳር የሌለው አጥሚት ገንዘብ ስላልነበረን እንበላ እንደነበር ረሳሽው?

***KW END***

**5. NARRATOR:**

ይህ 25ኛ ክፍል “በነገራችን ላይ …” ይሰኛል። የሚጀምረውም በእነ ምህረት ቤት እናቷ ወ/ሮሉሊት እጅግ በስራ ተጠምደው ሳለ ነው።

**SCENE 1: አቶ ሙላቱ VISITS ወ/ሮሉሊት AT HOME**

**6. ATMO: TANDIKA, INSIDE ምህረት HUT, DAYTIME**

**7. SFX: VEGETABLES BEING PACKED IN PLASTIC BAGS**

**8.** ወ/ሮሉሊት: **(to herself)** በፍጥነት እነዚህን አትክልቶች ማሸግ አለብኝ። ሆ! ካረፈድኩ ደንበኞቼ ያጉረመርማሉ!

**9. SFX: KNOCK ON THE DOOR**

**10.** ወ/ሮሉሊት **(to herself)** ማን ሊሆን ይችላል?) **(shouts)** ይግቡ!

**11. SFX: DOOR SLOWLY OPENING**

**12.** አቶ ሙላቱ: **(shyly)** ሉሊት፣ ባለቤቴ እንዴት ነሽ …

**13. SFX: TWO FOOTSTEPS**

**14.** ወ/ሮሉሊት: **(coldly)** ሙላቱ፤ እዚህ ምን ትሰራለህ? እዚህ ቤት ውስጥመልካም አቀባበል እንደሌለህ ፖሊስ ጣቢያ አልተነገረህም እንዴ?

***KW BEGIN***

**15.** አቶ ሙላቱ: **(desperate)** ግን ሉሊት፣ ይህ እኮ ቤቴ ነው። ምህረት እና ወንዶቹ ልጆች ልጆቼ ናቸው። ወደ ራሴ ቤት እንዳልገባ እንዴት ልትከለክይኝ ትችያለሽ?

**16.** ወ/ሮሉሊት: **(sarcastic)** የአንተ ቤት? ባለፈው ጊዜ ሳጣራ የቤቱን ኪራይ እየከፈልኩ እንደነበረ በኩራት ልጆቼ ብለህ የምትጠራቸውን ልጆችንም ስቀልብ እንደቆየሁ አረጋግጫለሁ። እና ይህን ለማድረግ ደግሞ አንዳቸውንም አልሸጥኩም።.

***KW END***

**17.** አቶ ሙላቱ: የእኔ ባለቤት፣ እባክሽ ሴት ልጃችንን ለአቶ መኩሪያ በመሸጤ አዝናለሁ። ግን መልሰን ልጅቷን የማግኘት እድል እንዳለን ተናግረዋል።

**18.** ወ/ሮሉሊት: ይቅርታ- እኛ?! እንድታውቀው ያህል፤ ሴት ልጄን በእጄ እንዳስገባ ሲያደርጉኝ ያኔ ከ30 ሜትር ርቀት ውጪ ልትቀርባት አትችልም። ተረዳኸኝ?

**19.** አቶ ሙላቱ: ግን እኮ …

**20.** ወ/ሮ ሉሊት: **(cuts him short)** *ደግሞ* በነገራችን ላይ፣ ያልሸጥካት ሴት ልጅህ ነፍሰ ጡር ናት!

**21.** አቶ ሙላቱ: ምን? ምህረት ነፍሰ ጡር ናት። **(sighs)**

***KW BEGIN*** አየሽ? ሁል ጊዜም ሴት ልጆችን ማስተማር ጊዜ መግደል ነው እል ነበር! እድሉ በነበረን ጊዜ መዳር ነበረብን!

**22.** ወ/ሮሉሊት: የማይታመን ነገር! የፈለከውን ሁሉ ካደረግህ በኋላም እንዲህ ትናገራለህ? **(clicks her tongue)**

***KW END*** ደግሞም ድንገት ከረሳሽው የሸጥከው ሴት ልጃችንን ብቻ አልነበረም። ሁለቱ ወንዶች ልጆቻችንንም ለእህትህ ወይዘሮ ለምለም ሰጥተሀት በማዕድን ስፍራ እንዲሰሩ ልካቸው ነበር! በእነርሱ ላይ ስላደረገችው ነገር በመክፈሏ ደስተኛ ነኝ። ብሩክ እዛ ሳለ በያዘዉ በሽታ ምክንያት ሊሞት ደርሶ ነበር። ቅዱስም ሌሊቱን ሁሉ ሲቃዠ ነዉ የሚያድረዉ።

**23.** አቶ ሙላቱ: ሉሊት፣ እባክሽን…

**24.** ወ/ሮሉሊት: ሂድልኝ፣ ሙላቱ፣ ፖሊስ ከመጥራቴ በፊት ሂድልኝ።

**25.** አቶ ሙላቱ: **(sighs)** እሺ

**26.** ወ/ሮሉሊት: ተመልሰህም እንዳትመጣ!

**27. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 2: ብሩክ, ቅዱስ AND ሙሴ RETURN FROM UPCOUNTRY**

**28. ATMO: MOVING TRUCK, LIGHT TRAFFIC ON COUNTRY ROAD**

**29. ብሩክ:** ሙሴ ከተማ ከመድረሳችን በፊት በአንተ የጭነት መኪና ምን ያህል ርቀት መጓዝ ይኖርብናል?

**30. ቅዱስ:** **(excited)** ብሩክ፣ አውቃለሁ! እኔ አውቃለሁ! የኪዱን ከተማ አልፈን ልክ ድልድዩን እ ንደተሻገርን ከተማው ውስጥ እንገባለን። ልክ ነኝ፤ ሙሴ?

**31. ሙሴ:** **(chuckles)** ሙሉ ለሙሉ አይደለም፣ ቅዱስ። ከኪዱ በፊት ሶስት ከተማዎች ማለፍ አለብን። አሁን የምታውቀው መስሎኝ ነበር። ከገጠር የእናትህን አትክልት ለማምጣት ብዙ ጊዜ ተመላልሰናል።

***KW BEGIN***

**32. ብሩክ:** ሙሴ በዚያ መንገድ ላይ ዘራፊዎች የሉም?

**33. ሙሴ:** የሉም፣ ብሩክ፣ በዚህ መንገድ ረጅም ጊዜ ተመላልሻለሁ። ምንም ነገር አይቼ አላውቅም። ሌላው ደግሞ ሁል ጊዜም በጣም ከመጨለሙ በፊት ወደ ቤቴ መግባቴን እርግጠኛ እሆናለሁ። ስለእዚህ መፍራት አያስፈልግም…

**34. SFX: FAST MOVING TRUCK APPROACHES, HONKS AND OVERTAKES**

**35. ሙሴ:** **(shouts angrily at the driver)** ሄይ፣ ምን ሆነሀል? እዚህ ጋር መደረብ አይቻልም ይላል!

**36.** ብሩክ: **(excited)** ዋው! መኪናው እንዴት እንደሚፈጥን ተመልከት። ሙሴ፣ ፍጠን! ልክ ፊልም ላይ እንደሚያደርጉት ቅደማቸው።

**37.** ቅዱስ: **(excited)** ልክ ነው፣ ሙሴ! የእኛ መኪና ከዛኛው ይልቅ አዲስ ነው። ሊቀድመን አይችልም!

**38.** ሙሴ: አይሆንም፤ ልጆች ያ አደገኛ አነዳድ ነው። ሾፌሩ ገጭቶን ነበር። እንደነገርኳችሁ የደህንነት መጠበቂያ ቀበቷችሁን አስራችኋል?

**39.** ቅዱስ/ብሩክ: አዎ፣ ሙሴ፤

**40.** ቅዱስ: ሳድግ ልክ እንደ አንተ ነጋዴ መሆን እና እንደዚህች ቆንጆ መኪና መግዛት እፈልጋለሁ። እና ልክ እንደ አንተ በጥንቃቄ እነዳታለሁ።

**41.** ሙሴ: **(laughs)** አሀ፣ በፍጥነት ሀሳብህን ቀየርክ? ከጥቂት ሰከንዶች በፊት የመኪና እቅድምድም አሽከርካሪ መሆን ፈልገህ ነበር።

**42. THEY LAUGH**

**43. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: ወ/ሮ ዘውዲቱ TALKS TO ወ/ሮሉሊት AT THE MARKET</u>**

**44. ATMO: OPEN AIR MARKET ATMO**

**45. TRADER 1:** **(shouts in the background)** እዚህ ጋር ልብስ በርካሽ! ሳትከፍሉ መመልከት ትችላላችሁ፡፡ ብትሞክሯቸው እና ብታይዋቸውም አናስከፍላችሁም! ልብስ በርካሽ!

**46. TRADER 2:** ሃምሳ ሳንቲም! ጣፋጭ ብርቱካን ሃምሳ ሳንቲም! ትኩስ  አትክልትም አለ! **(FADE UNDER)**

**47. SFX: VEGETABLES CUT ON A BOARD**

**48.** ወ/ሮ ሉሊት: **(to herself, confidently)** የፈለጉትን ያህል ቢጮሁ እንደሆነ፣ የእኔ ጎመን ገና አሁን የተቀነጠሰ ነው! እና በዚህ ሰዓት ደንበኞቼ ይህንን እንደሚያውቁ እርግጠኛ ነኝ...

**49. CUSTOMER:** እንደምን ዋሉ ፣ የምህረት እናት!

**50.** ወ/ሮሉሊት ይመስገን ! ምን ያህል እስር ትፈልጊያለሽ?

**51. CUSTOMER:** ሁለት እስር ጎመን እና ሁለት ቲማቲም

**52.** ወ/ሮሉሊት**:** ጎመኑ የተቀነጠሰ ይሁን?

**53. CUSTONER:** አይ እራሴው እቀነጥሰዋለሁ

**54.** ወ/ሮሉሊት: እንደፈለግሽ የእኔ እመቤት.

**55. SFX: VEGETABLES BEING WRAPPED IN A PLASTIC BAG**

**56. SFX: BILLS BEING EXCHANGED**

**57.** ወ/ሮሉሊት**:** ይኸውልሽ፤ መልስሽም ይኸው፡፡

**58. SFX: COINS JINGLE**

***KW BEGIN***

**59. CUSTOMER:** አመሰግናለሁ የምህረት እናት፡፡ የአንቺ አትክልቶች ሁሌም ጣፋጭ ናቸው፡፡ ግን የምታመጪው ትንሽ ነው! በመጣሁ ቁጥር ጨርሰሽ ነው የማገኝሽ፡፡

**60.** ወ/ሮሉሊት: **(laughs)** መልካም፣ ስራውን የጀመርነው ቅርብ ጊዜ ነው፡፡ ግን ሙሴ እና ልጆቼ አሁን ከማሳ የተቆረጠ  አትክልት ይዘው እየመጡ ነው፡፡

**61. CUSTOMER:** ይህማ መልካም ዜና ነው…

***KW END***

**62. SFX: VEHICLE APPROACHES AND COMES TO A STOP**

**63. CUSTOMER:** **(startled, screams)** ሄይ፣ አንቺ በዚህ መኪናሽ የምትጨፈልቂውን እያየሽ ሂጂ! እዚህ ጋር ቆሜ አልታይሽም?

**64. SFX: WINDOW ROLLS DOWN**

**65.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : **(from the car)** ይቅርታ እመቤት፡፡ ልገጭዎት አልነበረም፡፡ የማቆሚያ ቦታ እየፈለግሁ ነበር፡፡ ቦታው ተጨናንቋል፡፡  ሉሊት የምትባል ሴት እየፈለግሁ ነው፡፡ እዚህ አትክልት እንደምትሸጥ ተነግሮኛል፡፡ ታውቂያት ይሆን?

**66. CUSTOMER:** ኧረ እኔ  አላውቅም፤ ሉ… ፡፡

**67.** ወ/ሮሉሊት: እኔ ነኝ፡፡.

**68. CUSTOMER:** ውይ! ስምሽ ሉሊት መሆኑን አላውቅም። ማለቴ ሁሌም የምህረት እናት ብለን ነው የምንጠራሽ።

**69.** ወ/ሮሉሊት: (to ወ/ሮ ዘውዲቱ ) ምን ያህል እስር ትፈልጊያለሽ?

***KW BEGIN***

**70.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : ጎመን አልፈልግም......

**71.** ወ/ሮሉሊት: ትኩስ ቲማቲም እና ሽንኩርትም አለን። ቀንሼ ልሽጣቸው እችላለሁ።...

***KW END***

**72.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : ወ/ሮሉሊት፣ ይቅርታ፣ እዚህ ምንም ለመግዛት አልመጣሁም። መነጋገር እንችል እንደሆነ ብዬ ነው።.

**73.** ወ/ሮሉሊት: መነጋገር? ስለምን? አንተዋወቅም ።.

**74.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : ስሜ ዘውዲቱ ይባላል። ባለቤትሽ እኛ ጋር ይሰራ ነበር። አሁን ከፖሊስ ጣቢያ ከተለቀቀ ጊዜ አንስቶ እኛ ጋር እየኖረ ነው።.

**75.** ወ/ሮሉሊት: አሃ! አንቺ ዘውዲቱ ነሻ? ህምም... ሙላቱ ከእኔ ምንድን ነዉ የሚፈልገዉ ? ከእኛ እንዲርቅ አስቀድሜ ነግሬዋለሁ።

**76.** ወ/ሮ ዘውዲቱ እባክሽን፣ ወ/ሮ ሉሊት፣ መኪና ውስጥ አንዴ ግቢ። ለብቻችን እንነጋገር።

.

**77.** ወ/ሮሉሊት: እዚህ ጋር ምን እየሰራሁ እንደሆነ አይታይሽም? ይህንን ሁሉ እቃ ያለ ጠባቂ ልተወው አልችልም።

**78.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : እሺ አትጨነቂ። እዚሁ ጋር ማውራት እንችላለን። ወደ ሌላ ቦታ አልሄድም-መኪናው ውስጥ ሆነሽ እቃሽን መጠበቅ ትችያለሽ።.

79. **CUSTOMER:** የምህረት እናት እኔ ልጠብቅልሽ እችላለሁ። ግቢና ሴትዮዋ ምን እንደምትልሽ ስሚያት።.

80. ወ/ሮሉሊት: **(reluctantly)** መልካም...እሺ። ግን ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ፤ ዋጋቸውን ታውቂያለሽ?

81. **CUSTOMER:** በደንብ እንጂ፤ ብዙ አታስጠብቂያት። ሂጂ!

82. **SFX: FOOTSTEPS ወ/ሮ ሉሊት**

83. **SFX: CAR DOOR OPENS AND CLOSES**

84. **MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 4: ምህረት IS NOT FEELING WELL**

85. **ATMO: TANDIKA, INSIDE ምህረት HUT, DAYTIME**

86. ምህረት**: SNORES**

87. **SFX: DOOR OPENS**

88. **SFX: FOOTSTEPS - ወ/ሮሉሊት ENTERS**

89. ወ/ሮሉሊት: ሃይ ምህረት፣ ተነሽ እንጂ! አልጋ ላይ ምን ትሰሪያለሽ? ቅዳሜ ስለሆነ ብቻ ቀኑን ሙሉ መተኛት አለብሽ ማለት አይደለም! ለሰዓታት ስፈጋ ነበርኩ!

90. ምህረት**:** **(wakes up, lazily)** እንደምን ዋልሽ እማዬ። መጥተሻል?

91. ወ/ሮሉሊት**:** ምህረት ለምን ምግብ አልሰራሽም?

**92.** ምህረት: **(lazily)** ጤንነት አልተሰማኝም ነበር። ዶክተር ሮቤልን ደግሜ ሳገኘው ስለዚህ ነገር መንገር ያስፈልገኛል።.

***KW BEGIN***

**93.** ወ/ሮሉሊት: ለምን? ችግሩ ምንድን ነው?

**94.** ምህረት: ድካም እና ዝለት ይሰማኛል።

**95.** ወ/ሮሉሊት: ነይ፣ አትስነፊ! የትኛዋም ነፍሰጡር ሴት የሚሰማት ስሜት ነው። ልጆቹ ምግብ ስጡን ብለው ከመጮኻቸው በፊት አግዢኝ እና እናዘጋጅ።.

**96.** ምህረት: **(groans as she stands)** ኡፍ

***KW ED***

**97.** ወ/ሮሉሊት: አባክሽ ነይ ምህረት! ገና የስምንት ወር ነፍሰጡር ነሽ! አሁንም ልታግዢኝ ትችያለሽ! እነዚህን ቲማቲሞች ቁረጪልኝ።

**98. SFX: SHUFFLING FOOTSTEPS -** ምህረት

**99. SFX: PLATE AND PLASTIC BAG BEING PLACED ON TABLE**

**100. SFX: TOMATOES CUT SLOWLY**

**101.** ወ/ሮሉሊት: እሺ በይ፤ ማን ሊፈልገኝ እንደመጣ ገምቺ.

**102.** ምህረት: ማን መጣ?

**103.** ወ/ሮሉሊት: ወ/ሮ ዘውዲቱ.

**104.** ምህረት: የክፍል ጓደኛዬ የንጉሴ እናት? ምን ትፈልጋለች?

**105.** ወ/ሮሉሊት: **(sarcastically)** ያቺ እብድ ሴትዮ የወንድሞችሽን የትምህርት ቤት ክፍያ መክፈል ትፈልጋለች! አባትሽ አሁን ከእነርሱ ጋር እየኖረ ነው ብላለች፤ አይገርምሽም?

**106.** ምህረት: **(happily)** ምን? እማዬ፣ በጣም ጥሩ ዜና ነው፡፡ ቅዱስ እና ብሩክ በጣም ይደሰታሉ፡፡ እሺ እንዳልሻት ተሰፋ አደርጋለሁ፡፡

**107.** ወ/ሮሉሊት: አንቺም እንደ ሴትዮዋ እብድ ነሽ ልበል? የእርሷን በጎ አድራጎትማ ንክች አላደርጋትም፡፡ ገንዘቧን ለእራሷ እንድታደርገው ነገርኳት፡፡

***KW BEGIN***

**108.** ምህረት: **(taken aback)** ለምን እንደዚህ አደረግሽ? ብሩክ እና ቅዱስ ትምህርት ቤት መሄድ ይፈልጋሉ፡፡.

**109.** ወ/ሮሉሊት: አንድ ቀን ቅዱስ እና ብሩክ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ፡፡ ያን ሁሉ ካደረገኝ በኋላ ከአባትሽ አዲስ ጓደኞች ገንዘብ እንድቀበል ትጠብቂያለሽ?

**110.** ምህረት: **(struggles to catch her breath)** ግን እማዬ አባቴ የተሻለ ሰው ለመሆን እየጣረ እንደሆነ አይታይሽም?

***KW END***

**111.** ወ/ሮሉሊት: አሁን ገንዘብ እየቆጠብኩ ስለሆነ እራሴ ልጆቼን ትምህርት ቤት አስገባቸዋለሁ፡፡

**112.** ምህረት: **(breathing with difficulty)** ያታድያ መቼ ነዉ የሚሆነዉ?

**113.** ወ/ሮሉሊት: ምህረት ደህና ነሽ፣?

**114.** ምህረት: ይሻለኛል፣ እንደገና ትንሽ ጋደም ብል ሳይሻለኝ አይቀረም እማዬ፣ አባክሽን ወ/ሮ ዘውዲቱ ጋር መሄድ እና ይቅርታ ጠይቀሽ የሰጠችሽን መቀበል ይኖርብሻል። ጥሩ ሰው ትመስላለች። ልክ እንደ ልጇ ንጉሴ።

**115.** ወ/ሮሉሊት: አይሆንም ብዬሻለሁ! ድሆች ብንሆንም ለማኞች ግን አይደለንም…

**116. SFX: THUD AS ምህረት FALLS DOWN**

**117. SFX: UTENSILS (PLATE, PAN, ETC.) DROP**

**118.** ወ/ሮሉሊት: **(urgently)** ምህረት! ምህረት፣ ደህና ነሽ? **(slaps her cheeks)**

**119. SFX: SLAPS ON CHEEKS**

**120.** ወ/ሮሉሊት: ምህረት! ምህረት! ወይኔ በሞትኩት፤ እንዴ…በጣም ታተኩሳለች

**121. <u>OUTRO – NARRATOR:</u>**

ምህረትን ምን ገጠማት? ይሻላት ይሆን? የምህረት ጓደኞች ትዕግስት እና አልማዝስ? ለተወሰነ ጊዜ ስለእነርሱ አልሰማንም። ግን አሁን በቅርቡ በዚህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በተሰኘው ተከታታይ ድራማ የመጨረሻ ክፍል መልሱን እናገኛቸዋለን። ስለእዚህ በሚቀጥለዉ የመጨረሻዉን ክፍል ድራማ ማድመጣችሁን እንዳትዘነጉ። እንደተጣሉት…የዛሬዉን ድራማ አለያም ከእዚህ በፊት ያመለጣችሁን ክፍል በድጋሚ ማድመጥ ከፈለጋችሁ በድረ-ገጽ አድራሻችን **dw.de/lbe** ላይ ታገኙታላችሁ። በፌስ ቡክ ገጻችን ላይም ሊከታተሉን እንደሚችሉ አይዘንጉ። ጤና ይስጥልን!